# ምሥራቅ አፍሪካ ከ1914-1960 ዓ.ም.፦ እራሷን የቻለች ቤተ ክርስቲያን እድገት

## የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት

ከ1914-1918 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ በአጠቃላይ የወንጌል ሥራ የታገደበት ወቅት ስለነበር፥ ለቤተ ክርስቲያን የጨለማ ጊዜ እንደሆነ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ ልብ ልንለው የሚገባ አንድ የተስፋ ምልክት ወዲያውኑ ጦርነቱ እንደተጀመረ ዩጋንዳ ውስጥ ታይቷል። ነሐሴ 8 ቀን 1914 ዓ.ም. ዳዊዲ ችዋ የቡጋንዳ ካባካ (ንጉሥ) ከሚሆንበት ሕጋዊ የዕድሜ ደረጃ ላይ ደረሰ፥ ማለትም አሥራ ስምንት ዓመት ሆነው። ኅዳር 7 ቀን ሕጋዊ የሆነው ባሕላዊ ሥነ-ሥርዓት ይፈጸም በነበረበት ቡዶ በተባለው ኮረብታ ላይ ተከናወነ። ስፍራው ከዋናው ከተማ 13 ኪሎ ሜትር ያህል ይርቃል። ካባካው ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን ቀደም ሲል ይደረግ ከነበረው ልማድ ሁሉ በመለየት የንግሥ ሥርዓቱ በክርስቲያናዊ አሠራር በዩጋንዳው ጳጳስ አማካይነት እንዲከናወን አደረገ። ይህ ሰው በመስከረም ወር አንዲት የተማረች ክርስቲያን ልጃገረድ በማግባት በልዕልትነት እንድትታወቅለት አድርጎ ነበር።

አሁን ታንዛኒያ የምትባለው የጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ፥ የጀርመን እጅግ ጠቃሚ ቅኝ ግዛት ነበረች። ጦርነቱ በ1914 ዓ.ም. በተጀመረ ጊዜ፥ ጀርመኖች ታንዛኒያን ለመጠበቅ ታላቅ ጥረት አደረጉ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ጀርመኖች በቀላሉ ነው ከቶጎ፥ ከካሜሩንና ከደቡብ ምዕራብ አፍሪካ (የአሁኗ ናሚቢያ) የለቀቁት። ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ዋን ቮን ሊቶው ቮርቤክ በተባለው ሰው አመራር ስፍራውን ለመያዝና እስከ 1918 ዓ.ም. ድረስ ለመዋጋት ችለው ነበር። ይህ ረጅም ጦርነት በአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ብዙ ወታደሮች የሞቱበት ስለነበር፥ ምሥራቅ አፍሪካን እጅግ ዋጋ አስከፍሏታል።

በጦርነቱ ቀደም ያሉ ጊዜያት የእንግሊዝና የቤልጂግ ወታደሮች የታንዛኒያን የወደብ ክልል ያዙ። ይህ ሁኔታ በኪሊማንጃሮ ተራራና በማላዊ ሐይቅ አካባቢ የነበሩ የጀርመን ሚስዮናውያን ከመነሻው ጀምሮ በእንግሊዛውያን እጅ እንዲወድቁ አደረጋቸው። የእንግሊዝ ጦር

በአብዛኛው የጦርነት ወቅት የጀርመን ሚስዮናውያኑ በጣቢያዎቻቸው እንዲሠሩ ፈቅደውላቸዋል። በጦርነቱ መጀመሪያ ላይ ታንዛኒያ ውስጥ የሚሠሩ አንድ መቶ አምሳ የጀርመን ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያንና ብዙ የጀርመን ካቶሊኮች ነበሩ። እስከ 1916 ዓ.ም. ግን የእንግሊዝ ጦር ጀርመናውያኑ በሁሉም የሚስዮን ጣቢያዎች እንዲቆዩ አልፈቅድ አሉ። በዚሁ መሠረት ጦርነቱ እስኪያበቃ ድረስ አንዳንድ ሚስዮናውያን እሥር ቤት ውስጥ ቆዩ። ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የእድገት ደረጃ ላይ በመሆኗ የደረሰባት ኪሣራ እጅግ ብዙ ነው። የሚስዮናውያን እጥረት ያኔም ነበር። በመሆኑም ጀርመናውያን ያልሆኑ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን አባላት እርዳታ ሊሰጧቸው ፈለጉ። በዚሁ መሠረት ቡኮባ በተባለው ስፍራ የሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር፥ የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮናዊ ተልእኮ ለማዕከላዊ አፍሪካ እና በስተደቡብ የሚገኙት ሁለት የስኮትላንድ ማኅበራት እርዳታ አደረጉ። አንዳንድ የአሜሪካ ሉተራውያን ኪሊማንጃሮ አካባቢ ለመሥራት በ1922 ዓ.ም. ወደ ስፍራው መጡ። በ1925 ዓ.ም. የጀርመን ማኅበራት ወደ ቀድሞ አካባቢዎቻቸው መመለስ ጀምረው ነበር። ይሁን እንጂ ጦርነቱና የጀርመን ሚስዮናውያን ለረጅም ጊዜ ከስፍራው መታጣት ራሷን ያልቻለችውን ቤተ ክርስቲያን እጅግ ጎዳት።

## ከ1918-1939

ከመጀመሪያው የዓለም ጦርነት በኋላ የጀርመን ምሥራቅ አፍሪካ በውክልና አስተዳደር ለእንግሊዝ ተሰጠ። በዚሁ መሠረት ሦስቱ የምሥራቅ አፍሪካ ክልሎች ዩጋንዳ፥ ኬንያና ታንጋኒካ በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ሥር ሆኑ። ፈረንሳውያን፥ ፖርቱጋሎችና ቤልጂጎች ቢያደርጉትም፥ እንግሊዛውያን ግን ለራሳቸው ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን (የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን) ለትምህርት ቤቶቻቸውም ሆነ ለሌላ ሥራ የተለየ ድጎማ አላደረጉላቸውም። በዚህ ፋንታ ያደረጉት፥ ለታወቁት ሚስዮናውያን ሁሉ እኩል የገንዘብ እርዳታ መስጠት ነበር። የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያን በፈረንሳይ፥ በቤልጂግና በፖርቱጋል አፍሪካ በተቃውሞና ድጋፍ በማጣት ሲጎዱ፥ በእንግሊዝ አስተዳደር ውስጥ የነበረችው የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ግን፥ ፕሮቴስታንቶች የሚያገኙትን ያህል እርዳታ ታገኝ ነበር።

ከ1918-1939 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበረው ትምህርት እንግሊዝ ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ የእድገት እቅድ የተከተለ ነበር። በ1923 ዓ.ም. የእንግሊዝ መንግሥት ባካሄደው ስብሰባ በቅኝ ግዛቶቹ ውስጥ የነበረውን የትምህርት ሁኔታ የሚቆጣጠር ኮሚሽን አቋቋመ። ይህ ኮሚሽን የፕሮቴስታንት፥ የሮም

ካቶሊክ ሚስዮናውያንና የመንግሥት ባለሥልጣኖች በአባልነት ነበሩበት። ከ1923 ዓ.ም. ጀምሮ ቅኝ ገዢ መንግሥታት ለሚስዮን ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ገንዘብ እና የትምህርቱን ደረጃ ከፍ አደረጉት። ብዙዎቹ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በትምህርቱ ጉዳይ ከመንግሥት ጋር በመተባበራቸው፥ የገንዘብ እርዳታ አገኙ። የሮም ካቶሊኮች ከእንግሊዝ መንግሥት ገንዘብ በማግኘታቸው በጣም ደስተኞች ነበሩ። በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩት የካቶሊክ ሚስዮኖች የትምህርት አማካሪ፥ ለሮም ካቶሊክ ሚስዮናውያን በ1928 ዓ.ም. ዳሬ ሰላም ውስጥ እንዲህ ብለዋቸዋል፦ "በሙሉ ኃይላችሁ ተባበሩ፥ ዋና ተግባራችሁ የሆነውን የወንጌል ሥራና የትምህርት ተግባራችሁን በጥምር ለማካሄድ በማትችሉባቸው ሥፍራዎች ትምህርት ቤቶቻችሁን በሚገባ ለመምራት ይቻላችሁ ዘንድ አብያተ ክርስቲያናችሁን ችላ በሏቸው።" ትምህርት ቤቶች ያላመኑ ሰዎችን ወደ ቤተ ክርስቲያን የማምጫ በጣም ጠቃሚ መንገዶች እንደሆኑ የሮም ካቶሊኮች ተረድተው ነበር።

ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበሩት ሚስዮናውያን፥ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቀጥሎ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርትን አስፈላጊነት በመገንዘብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ማቋቋም ጀመሩ። ከእነዚህ የመጀመሪያው፥ ኬንያ ውስጥ ያሉት ፕሮቴስታንቶች አንድነት ለመፍጠር ካደረጉት ጥረት የተገኘ ነው። የፕሮቴስታንት ሚስዮኖች ኅብረት በ1926 ዓ.ም. የአላያንስ ሃይ ስኩል የተባለውን መሠረቱ። ትምህርት ቤቱ ኩኩዩዎች አካባቢ ተመሥርቶ ታላቅ የክርስትና ትምህርት ማዕከል ሆነ። የሮም ካቶሊኮች በ1940 ዓ.ም. ማንጉ ወደተባለው ማዕከላዊ ክፍለ አገር የተዛወረውን የካባ ሃይ ስኩል በ1930 ዓ.ም. መሠረቱ። በታንጋኒካና በዩጋንዳም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚስዮን ማኅበራት ተከፍተዋል።

ከ1918-1923 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ኬንያ ውስጥ የነበሩት የውጭ ዜጎች፥ የእንግሊዝ መንግሥት ለእነርሱ የሚጠቅም ሕግ እንዲያወጣ ሊገፋፉት ሞከሩ። በ1919 የኬንያ ጠቅላይ ገዢ ለባለሥልጣናቱ ሁሉ ባሠራጨው ትእዛዝ አፍሪካውያን ነጮች በያዟቸው እርሻዎች ላይ፥ ቢያስፈልግ በኃይል እንዲሠሩ ደነገገ። ብዙ ሚስዮናውያን ይህን ትእዛዝ በማውገዝ፥ በፕሮቴስታንት ሚስዮኖች ትብብር በኩል ለእንግሊዝ መንግሥት ግልጥ ተቃውሟቸውን አሰሙ። በዚሁ መሠረትና እንግሊዝ ውስጥ በነበሩት የሚስዮን መሪዎች ጥረት፥ የቅኝ ገዢው መንግሥት ትእዛዝ ተሠረዘ። ኋላ በ1923 ዓ.ም. የሚስዮን መሪዎችና ኬንያ ውስጥ የነበሩ ሌሎች ሰዎች ካሳዩት ፍላጎት በመነሣት የእንግሊዝ መንግሥት የኬንያ አፍሪካውያን ፍላጎት ምን ጊዜም ከነጭ ሰፋሪዎች ፍላጎት መቅደም አለበት

የሚል ጽሑፍ (Devonshire White Paper/"ደቮንሻየር ዋይት ፔፐር") አሰራጨ።

ከ1918-1938 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ብዙ አዳዲስ የሚስዮን ማኅበራት ወደ ምሥራቅ አፍሪካ መጡ። ጥቂት ቀደም ብለን እንዳየነው፥ የአሜሪካ ሉተራውያን በ1922 ዓ.ም. ታንጋኒካ ውስጥ ሥራ ጀመሩ። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን በዚሁ ዓ.ም. ዩጋንዳ ውስጥ መሥራት ጀመረ። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ከቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጋር ባደረገው ስምምነት መሠረት ምዕራብ ናይል ዲስትሪክት ውስጥ ሠርቷል። እዚያ የተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያንም የዩጋንዳ ቤተ ክርስቲያን አካል ሆኑ። በ1921 ዓ.ም. የደኅንነት ሠራዊት የተባለው ቡድን ናይሮቢ፥ ቲካ፥ ማላኪሲ እና ኢምቡ በተባሉት ስፍራዎች ሥራ ጀመረ። እነዚህ ከጦርነቱ በኋላ ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ከገቡት ብዙ አዳዲስ ቡድኖች ሦስት ምሳሌዎች ብቻ ናቸው።

የሚስዮን ማኅበራት በሕክምና ረገድ ያደርጉት የነበረውን አስተዋጽኦ ቀጠሉ። ለታንጋኒካ ብዙ ስፍራዎች ያገለግል የነበረው ብቸኛ የህክምና ማዕከል የሚስዮን ሆስፒታል ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር፥ የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮናዊ ተልእኮ ለማዕከላዊ አፍሪካ፥ ሉተራውያን፥ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን፥ እና የሮም ካቶሊኮች የሆስፒታል ሥራ ያካሂዱ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር እና የሮም ካቶሊክ ሚስዮናውያን የሕክምና ሥራ በዩጋንዳ የጀመሩት በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ዓመታት ነው። በ1918 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር የአዋላጆች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ከፈተ። በ1971 ዓ.ም. መጨረሻ ዩጋንዳ ውስጥ ከነበሩት 16,400 የሆስፒታል አልጋዎች መካከል ከአምሳ በመቶ በላይ የሚሆኑት በቤተ ክርስቲያን ወይም በበጎ አድራጊ ድርጅቶች ይረዱ ነበር። የምሥራቅ አፍሪካን የስኮትላንድ ሚስዮን ኬንያ ሴንትራል ፕሮቪንስ ውስጥ በ1908 ዓ.ም. የመጀመሪያውን ሆስፒታል ሠራ። የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና ሌሎች ሚስዮኖች የሕክምና አገልግሎትን በመመሥረት ረገድ ንቁ ተሳትፎ ያደርጉ ነበር። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ከመነሻው ጀምሮ ባመቻው ጊዜ ሁሉ በሕክምና ሥራዎች ተሠማርቶ ነበር። ብዙዎቹ ጣቢያዎቹ የመድኃኒት ማደያ ነበራቸው። በአሁኑ ጊዜ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ኬንያ ውስጥ ሦስት ሆስፒታሎች አሏት። የምትሠራውም ኪጃቤ፥ ካፕስዋርና ሎኮሪ በሚባሉት ስፍራዎች ሲሆን፥ አሥራ ሁለት የሕክምና መስጫ ጣቢያዎች አሏት። ከ1918-1939 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በሁለት የምሥራቅ አፍሪካ ክልሎች የመማክርት ትብብሮች እድገት ታይቷል። ኬንያ ውስጥ የፕሮቴስታንት ሚስዮን በመጀመሪያ አንድ

የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት እንቅስቃሴ ሲያካሂድ፥ የተባበረ የሚስዮናውያን ምክር ቤት ለማቋቋምም ሙከራ አድርጎ ነበር። ኬንያ ውስጥ የሚሠሩ ዋና ዋና የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በ1908 ዓ.ም. ሚሲኖ በተባለው ስፍራ ስብሰባ አድርገው የተባበሩት አብያተ ክርስቲያን ኬንያ ውስጥ በመኖሩ ጉዳይ ላይ ተወያዩ። በ1913 ዓ.ም. በጉዳዩ ለመመካከር ኩኩዩ ውስጥ ጠቅላላ ስብሰባ ተጠራ። ስብሰባው ቶጎቶ በተባለ ስፍራ በሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር መሥሪያ ቤት ውስጥ የተደረገ ሲሆን፥ የተገኙት ተወካዮችም ከቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር፥ ከስኮትላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን፥ ከአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን፥ ከተባበሩት የመቶዲስት ሚስዮን፥ ከነጻ ናይሎቲክ ሚስዮን፥ ከሉተራውያን፥ ከአፍሪካ የጓደኞሞች ሚስዮን፥ ከሰባተኛው ቀን አድቬንቲስቶች፥ እና ከወንጌል ሚስዮናዊ ማኅበር የመጡ ናቸው። በጊዜው ከወንጌል እምነት መግለጫ ጋር የተዛመደ ሕግ ተጻፈ። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ተወካዮች እንደዚህ ወዳለው ኅብረት የሚገቡት ሕጉ ቤተ ክርስቲያን ለእውነተኛው ቅዱስ ቃልና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሆነው የደኅንነት ወንጌል በእውነት የምትቆም መሆኑን በግልጥ ያሳወቀ እንደሆነ ብቻ መሆኑን ገለጡ። በውይይቱ ጊዜ የተነሡት ብቸኛ አስቸጋሪ ነገሮች፥ ስለ ጥምቀት (ባፕቲስቶች ያነሡት) እና ስለ ክርስትና መቀበል ማረጋገጫ (እንግሊዛውያን ያነሡት) ነበሩ። ከዚያ በኋላ ሕጉ፥ ታላቅ ፍላጎት በታየበት ሁኔታ በአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን፥ በቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር፥ በተባበሩት የመቶዲስት ሚስዮን፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ከአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ጋር በተዋሀደው ነጻ የናይሎቲክ ሚስዮን ተፈረመ። ቀጥሎ በኬንያ የተባበሩትን አብያተ ክርስቲያን የመሠረቱት ድርጅቶች ተወካዮች የተካፈሉበት የጋራ ቅዱስ ቊርባን ፕሮግራም ተካሄደ። ከቅዱስ ቊርባኑ ፕሮግራም በኋላ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባላት፥ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን እና ሌሎች የእንግሊዝ ሚስዮን አባላት ያልሆኑ ሰዎች የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች መሆናቸውን ተቃወሙ። የአጥቢያ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባላት ጉዳዩን አስመልክተው ለካተንበሪው ሊቀ ጳጳስ ደብዳቤ ጻፉ። እርሱም ወደፊት በጋራ በሚካሄደው የቅዱስ ቊርባን ፕሮግራም እንደማይሳተፍ ኬንያ ለሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አስታወቀ። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር እና የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በኬንያ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ያደረጉት ጥረት የተሰናከለው በዚህ ሁኔታ ነበር።

በ1918 ዓ.ም. ኬንያ ውስጥ በሚገኙት የፕሮቴስታንት ሚስዮኖች መካከል ትብብር ለመፍጠር ሌላ ስብሰባ ተካሄደ። ሆኖም የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር፥ ከአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን፥ ከስኮትላንድ ሚስዮን

ቤተ ክርስቲያን፥ እና ከተባበሩት የመቶዲስት ሚስዮን ጋር በቅዱስ ቁርባን ጉዳይ ባሳየው ልዩነት ሳቢያ የተባበረች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት አልተቻለም። እንግሊዛውያን እንደገና በ1923 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያንን ትብብር አሰናከሉ። በዚህ ሳቢያ የፕሮቴስታንት ሚስዮኖች ኅብረት በከፋ ሁኔታ ተናጋ። ይህ የሆነው፥ ለዘብተኛነትን (Liberalism/ ሊበራሊዝም) አስመልክቶ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር በ1922 ዓ.ም. እንግሊዝ ውስጥ መከፋፈል በገጠመው ጊዜና ኬንያ ውስጥም የእንግሊዝ ሠራዊተ ክርስቶስ ማኅበር፥ እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ሚስዮናውያን ማኅበር የተባለው ድርጅት በተከፋፈሉበት ጊዜ ነው። በ1924 ዓ.ም. አንዳንድ እንግሊዛውያንና ሌሎችም፥ መሠረታዊ የእምነት ትምህርትን እና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ አዲስ አሳብ ወደ አላየንሱ አመጡ። በዚህ ጊዜ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን የተባለው ድርጅት ይህ አሳብ በ1913 ዓ.ም. እና በ1918 ዓ.ም. ከተደረገው ስምምነት መንፈስ ውጭ ነው በማለት ከአላየንሱ ወጣ። ድርጅቱ የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን የሥነ-መለኮት ጉዳይ በተብራራበት ወቅት እንደገና ወደ አላየንሱ ተመልሶ ነበር። ከ1932 ዓ.ም. ወዲህ ግን የማንኛውም ውይይት ተካፋይ አልሆነም። ሌሎች የኅብረቱ አባላት ግን አንዲት የተባበረች ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት መጣራቸውን ቀጠሉ። በዚሁ መሠረት ስድስት ዓመታት የፈጀ ስብሰባቸውን በ1961 ዓ.ም. ጀመሩ። ተሰብሳቢዎቹ፥ ኬንያና ታንዛኒያ የሚገኙ እንግሊዛውያን፥ ፕሬስቢቴሪያኖች፥ መቶዲስቶች፥ ሉተራውያን እና ኬንያና ታንዛኒያ ውስጥ ያሉ ሞሬቪያኖች ነበሩ። ያም ሆኖ አንዲት የተባበረች ቤተ ክርስቲያን ሊመሠርቱ አልቻሉም። ይህ ሁኔታ ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ አንዲት ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት (Ecumenicalism/ኤኪዩሚኒካልዝም) ያኔ ያልተቻለ መሆኑን የሚያመለክት ይመስላል።

በ1924 ዓ.ም. አላየንሱ ውስጥ ያሉትንም ሆነ የሌሉትን ጨምሮ የኬንያ የሚስዮናውያን መማክርት ተቋቋመ። በ1944 ዓ.ም. የኬንያን የሚስዮናውያን መማክርት በመተካት የኬንያ ክርስቲያን መማክርት ተመሠረተ። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን እና የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የኬንያ ክርስቲያን መማክርት ሕጋዊ አባላት ነበሩ። የአዲሱ የመማክርት ጉባኤ የኬንያ ክርስቲያን መማክርት ሥራ በኤኪዩሚኒካል እንቅስቃሴ ምክንያት እንዳይተጓጎል ለመከላከል አባላቱ የየትኛውም ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል እንዳይሆኑ መወሰኑን በግልጥ አሳወቀ። ዩጋንዳ ውስጥ የሚገኘው የፕሮቴስታንት ሚስዮን ለረጅም ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ብቻ ስለነበር፥ እንደ ኬንያ የሚስዮን መማክርት ወይም የኬንያ ክርስቲያን መማክርት ያለ አንዳችም ኅብረት እዚያ አልነበረም።

በ1937 ዓ.ም. የታንጋኒካ ሚስዮናዊ መማክርት ታንጋኒካ ውስጥ ተመሠረተ። በ1948 ዓ.ም. የታንጋኒካ ክርስቲያናዊ መማክርት ተባለ። በኋላ ደግሞ የታንዛኒያ ክርስቲያናዊ መማክርት ተብሎ ተሰየመ። ምክር ቤቱ በሥራውና በዓላማው ከኬንያ ክርስቲያን መማክርት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነበር።

ወደ ሌላ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽታ ዞር ስንል በ1929 ዓ.ም. እና 1930 ዓ.ም. ኬንያ ማዕከላዊ ክፍል ውስጥ የግርዘት ጭቅጭቅ መፈጠሩን እንመለከታለን። ጥያቄው ሴቶች ልጆች ይገረዙ ዘንድ በነገድ ሽማግሌዎች ሊገደዱ ይገባል ወይ? የሚል ነበር። ይህ ጥያቄ የተነሣው፥ ከ1929 ዓ.ም. በፊት ነው። ከስኮትላንድ ቤተ ክርስቲያን የመጡ ሚስዮናውያን ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ የሴቶችን መገረዝ በመቃወም ያስተምሩ ነበር። የተሰጠው ምክንያት በግርዘቱ ጊዜና ከዚያም በኋላ የሚፈጠረውን ችግር የሚመለከት የሕክምና ጉዳይ ነው። ይህ ትምህርት በ1912 ዓ.ም. ሚስዮን አዳሪ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚማሩ ልጃገረዶች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ጀመረ። በሰኔ ወር 1914 ዓ.ም. ሁለት ልጃገረዶች ለመገረዝ ያለመፈለጋቸውን ገለጡ። ነገር ግን ሚስዮናውያኑም ሆኑ አምነው የተጠመቁ አነስተኛ የማኅበረሰብ መሪዎች ይህን ልማድ በግልጥ አንቀበልም ለማለት ጊዜው እንዳልሆነ ተሰማቸው። ይህ ተግባር ኩኩዩ ሆስፒታል ውስጥ በእርዳታ ሰጪ ክርስቲያኖች ኃላፊነት በተለመዱት ገራዦች እንዲፈጸም ልጃገረዶቹ፥ ወላጆቻችውና ግርዙቱን የሚፈጽሙት ሰዎች ተስማሙ። በዚሁ መሠረት በ1915 ግርዙቱ ተፈጸመ። በዚህ ጊዜ አንዲት ልጃገረድ ከፍርሃት የተነሣ መገረዙን አልፈለገችም ነበር። እንደፈራችውም በስለቱ ተጎዳች። በዚህ ሳቢያ ሆስፒታሉ ውስጥ ይደረግ የነበረው ሙከራ ተቋረጠ። ቱሙቱሙ በተባለ ስፍራም ተመሳሳይ ሙከራ ተደርጓል። በ1915 ዓ.ም. ሦስት ልጃገረዶች በባሕላዊ ገራዥ ተገረዙ። የግርዛቱን ሁኔታ በዓይናቸው ያዩት ዶክተር ፊሊፕ የተባሉ ሰው ድርጊቱ እጅግ ከባድ የጭካኔ ሥራ ሆኖ ስላገኙት፥ ግርዘት ይታገድ ዘንድ ባመቺው መንገድ ሁሉ ይቃወሙ ጀመር። ይህም አብያተ ክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ፖሊሲ እንዲመረምሩ አደረጓቸው። በዚሁ መሠረት መጋቢት 1916 ዓ.ም. በኩኩዩና ቱሙቱሙ ውስጥ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ኮሚቴዎች፥ የተጠመቁ ልጃገረዶች የክርስቲያን ቤተሰብ ሴት ልጆች ወይም ሚስዮን ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ሴት ልጆች ግርዘት ጉዳይ የቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ሐሳብ አቀረቡ። ካምቡዊ ውስጥ በሚገኘው የወንጌል ሚስዮን ጣቢያ፥ ኪጃቢ የሚገኘው የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ጣቢያና ካቤቴ የሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጣቢያዎች ተመሳሳይ አቅጣጫ የተከተሉ ይመስላል።

ከ1916-1929 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ አብያተ ክርስቲያን የሴት ልጅን ግርዘት በመቃወም ማስተማራቸውን ቀጠሉ። በመጋቢት ወር 1929 ዓ.ም. ሴንትራል ፕሮቪንስ ውስጥ ያሉ አያሌ የእምነት ክፍሎች በችግሩ ላይ ለመወያየት ቱሙቱሙ እተባለው ስፍራ ተሰበሰቡ። በስብሰባው ፍፃሜ፥ ድርጊቱ ክፉና ክርስቲያኖች ሊፈጽሙት የማይገባ ስለመሆኑ ተስማሙ። ከዚህ በኋላ በሰኔ ወር 1929 ዓ.ም. ካምቡዊ በተባለ ትምህርት ቤት የምትማር አንዲት ልጃገረድ መንገድ ላይ ታፍና በግድ ተገረዘች። ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ቢወሰድም ዳኛው በክርስቲያኖች ላይ ፈረደ። ከዚያ በኋላ የነገድ ሽማግሌዎች ማንኛይቱንም ሴት ልጅ በግድ ሊገርዟት ይችላሉ ተብሎ ደነገገ። የኩኩዩ ማዕከላዊ ማኅበር ይህን የልማድ ግርዛት ሲደግፍ፥ የቤተ ክርስቲያን አባላት ተቃወሙት። ውዝግቡ የገጠር ነዋሪዎችን አስቆጣ። ወዲያውኑ የታየው ውጤት በሚስዮን ሥራ ላይ ከባድ ችግር መፈጠሩ፥ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን የሚሳተፈው ሕዝብና የተማሪዎች ቁጥር መቀነሱ ነበር። የረጅም ጊዜ ውጤቱ ከዚህም የከፋ ሆነ። በ1929 ዓ.ም. በኩኩዩላንድ የተዘራው ሰፊ የመለያየት መንፈስ የተነጠሉ ነጻ አብያተ ክርስቲያን እንዲመሠረቱ ምክንያት ሆነ።

"የግርዘት ውዝግብ" በአንዲት አነስተኛ የምሥራቅ አፍሪካ ክፍል የተወሰነ ቢሆንም፥ በ1929 ዓ.ም. ግን ራቅ ባለው ምዕራባዊ ክፍል በመዛመት በፍጥነት ክልሉን አዳረሰው። ከ1910-1930 ዓ.ም. ባለው ጊዜ በብዙ የምሥራቅ አፍሪካ ክፍሎች ክርስትና "የብዙሃን እንቅስቃሴ" ሆኖ ነበር። ማለት ብዙ ሕዝቦች ክርስቲያን ለመሆን በአንድነት እየወሰኑ ወደ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ወይም ሌሎች ሚስዮኖች በመሄድ እራሳቸውን ለጥምቀት ያቀርቡ ነበር። ሚስዮናውያን መጋቢዎች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኝ የማወቅን አስፈላጊነት እንዲያምን ባደረጉት ጥረት፥ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑ ብዙ ሰዎች ሊያሰባስቡ ቢችሉም ሰዎቹ ግን በርግጥ የዳኑ አልነበሩም። በ1928 ዓ.ም. ሩዋንዳ ውስጥ ከእንግሊዝ ሚስዮን ጋር ይሠሩ የነበሩ ሁለት የዩጋንዳ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ አማካይነት በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘው ሙሉ ደኅንነት እንደሚያስፈልጋቸው ተገነዘቡ።

በዚሁ መሠረት ዶክተር ጆ ቸርች በተባለ ሚስዮናዊ አማካይነት ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ሰላም መሠረቱ። ከዚያ በኋላ ቀደም ሲል የሠሯቸውን ኃጢአቶችና የተሳሳቱ ድርጊቶች በሕዝብ ፊት ይናዘዙ፥ ሰዎችም ለውጣቸውን ይመለከቱ ጀመር። የመጀመሪያው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የተጀመረው፥ በመጋቢት ወር 1928 ዓ.ም. ሩኪንጋ በተባለ ስፍራ ቢሆንም እንቅስቃሴው ለረጅም ጊዜ አልቆየም። በመሆኑም ለእውነተኛ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ያለማቋረጥ ይጸልዩ ዘንድ እንግሊዝ

ውስጥ ለሚገኙ ደጋፊዎች ጥያቄ ተላከላቸው። የጸሎቱ ሰፊና ጥልቅ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የጀመረው በታኅሣሥ ወር 1933 ዓ.ም. ነበር። ይህ ‹‹ሩዋንዳይዝም››፥ ‹‹ባሎኮሌ››፥ ‹‹የዳኑት››፥ ወይም ‹‹ዋንዱኑ›› በመባል የሚጠራውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ አስከተለ።

ሩኪንጋ የጀመረው ይህ እንቅስቃሴ ሩዋንዳ እና ዩጋንዳ ውስጥ ተጠናከረ። በደቡብ በኩል ደግሞ ቡሃያ እስከተባለው ስፍራ፥ ታንዛኒያ እስከሚገኘው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አካባቢዎች፥ እንዲሁም በሰሜን ወደ ኬኒያ ሱዳን፥ በምሥራቅ ወደ አንግሊካውያንና ፕሬስቢተሪያን ኩኩዩዎች ወደነበሩበት አካባቢ ተስፋፋ። ዝቅተኛ ውጤት ያሳየው ካቶሊካውያንና የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን እንዲሁም የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮናዊ ተልእኮ ለማዕከላዊ አፍሪካ የተባለው ቡድን አባላት በሰበኩባቸው አካባቢዎች ነው። መንፈሳዊ እንቅስቃሴው በአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን አብያተ ክርስቲያን ያላደገበት እርግጠኛ ምክንያት፥ ሚስዮናውያኑና መጋቢያን አንድን ሰው የቤተ ክርስቲያን አባል ከማድረጋቸው በፊት ሰውዬው ኃጢአቱን መናዘዝና ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ያለበት መሆኑን አጥብቀው ይናገሩ ስለነበር ነው። በመሆኑም በ1930ዎቹ ዓ.ም. አፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩት ዓለማዊ ክርስቲያኖች ምናልባት በሌሎቹ አብያተ ክርስቲያን ካሉት ጋር ሲነጻጸሩ በጣም ጥቂት ነበሩ። መንፈሳዊ እንቅስቃሴው፥ ሰዎች ደኅንነትን በግል መለማመድ አለባቸው የሚል የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ ስለነበር፥ ካቶሊኮች ያልተቀበሉት መሆኑ እርግጥ ነው። የዩኒቨርስቲዎች ሚስዮናዊ ተልእኮ ለማዕከላዊ አፍሪካ ‹‹በቅዳሴ ላይ የሚያተኩር ቤተ ክርስቲያን›› እንደመሆኑ መጠን፥ የእንግሊዝ ሚስዮን ለግል ደኅንነት አስፈላጊነት ብዙም ትኩረት አልሰጠውም ነበር።

የመንፈሳዊው እንቅስቃሴ የመጀመሪያ መልእክተኞች በ1937 ዓ.ም. ኬንያን ጎበኙ። ይህ የመልእክተኞች ቡድን ካቤቴ በተባለው አካባቢ ለነበሩ ክርስቲያኖች በመስበክ ለብዙ ጊዜ ቆየ። የቡድኑ አባላት ተልዕኳቸውን ፈጽመው ከመሄዳቸው በፊት ጥቂት ክርስቲያኖች፥ ታዋቂ የእንግሊዝን ካህናትን ጨምሮ ጥልቅ የደኅንነት ስሜት ተሰማቸው። በ1938 ዓ.ም. አካባቢ ከሩዋንዳ የመጣው ሁለተኛ የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ መልእክተኞች ቡድን ኬንያን ጎበኘ። በጉብኝቱ ወቅትም ናይሮቢ በሚገኘውና ፑምዋኒ በተባለው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ጣቢያ ከቀድሞው የላቀና የተሳካ የስብከት አገልግሎት አበረከተ። መንፈሳዊ እንቅስቃሴው ባደገ ቁጥር መልካም ያልሆኑ አንዳንድ ነገሮች ያቆጠቁጡ ጀመር። ይህ እንቅስቃሴ በኃጢአት ኑዛዜ ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ፥ ብዙ ሰዎች የሚናዘዙት ነገር ፍለጋ ወደ ዓለማዊ ኑሮ

መመለሱ ተገቢ ይመስላቸው ጀመር። እንዲሁም አንዳንድ የወንጌላውያን ቡድኖች ድርጊትና ባሕርያቸው መሆን እንደሚገባው አልነበረም። በመሆኑም በ1947 ዓ.ም. የመንፈሳዊ እንቅስቃሴው ኅብረት (Revival Fellowship/ሪቫይቫል ፌለውሺፕ) ክርስቲያኖችን ለመርዳት በማሰብ ለብዙ ቀናት የሚቆዩ ጠቅላላ ስብሰባዎች ያካሂድ ጀመር። ስብሰባዎቹ ከ3,000-30,000 የሚደርሱ ሰዎችን ስበዋል። መንፈሳዊ እንቅስቃሴው በአደረጃጀቱ ከተለመዱት የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር መዋቅሮች ይለይ ነበር። ባለሥልጣናት፥ ሥራ አስፈጻሚዎች፥ የሚከፈላቸው ሠራተኞች፥ ዋና መሥሪያ ቤቶች፥ ቢሮዎች፥ ቢሮክራሲዎች፥ የወረቀት ሥራ፥ ቃለ ጉባኤዎች፥ በጀት፥ የአባላት ዝርዝርና ዓመታዊ መዋጮዎች አልነበሩትም። አንድነቱ፥ አባላቷን ያቀፈች ቤተ ክርስቲያን የምታደርገው ዓይነት ያልሆነ፥ በመዋቅር ያልተቀናበረ፥ ድንገተኛና በቡድን የተመራ ነበር።

ከ1918-1939 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ደቡብ ሱዳን ውስጥ እድገቱ ቀጠለ። ነገዶቹ እጅግ በየስፍራው ተሰራጭተው ስለነበር፥ ሥራው ቀስ በቀስ ነበር የሚስፋፋው። ያም ቢሆን በ1906 ዓ.ም. ሥራውን የጀመረው የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባላት ጥረታቸውን በብርታት ቀጠሉ። የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር ይሠራ የነበረው፥ ሞሩ በተባለ ነገድ ውስጥ ነበር። በ1926 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ ስምንት የሞሩ ነገድ አባላት የሆኑ ወንዶች ልጆች በተጠመቁ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ አማኞች ተገኙ። በ1930 ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ አምስት የነገዱ ክርስቲያን ሴቶች ተጠመቁ። በ1934 ዓ.ም. 125 የተጠመቁ አባላትን ጨምሮ፥ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ 414 ደርሶ ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራዎችም ቀጠሉ። በዚሁ መሠረት ገና ሕጻን የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የማርቆስን ወንጌል በ1928 ዓ.ም.፥ የሉቃስን ወንጌልና የሐዋርያትን ሥራ በ1931 ዓ.ም.፥ የዮሐንስን ወንጌል በ1934 ዓ.ም. በቋንቋዋ አገኘች። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ደቡብ ሱዳን ውስጥ ሥራውን የጀመረው በ1949 ዓ.ም. ነው። ሚስዮኑ አንድ የውኃ ጉድጓድ እንደቆፈረ ወዲያውኑ አንድ የሚስዮን ጣቢያ ይመሠረት ነበር። የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ደቡብ ሱዳን ውስጥ መመሥረት ከኮንጎ የመጡ ክርስቲያኖች አገልግሎት ውጤት ነበር። ደቡብ ሱዳን ውስጥ የነበረው ሥራ ቀደም ሲል በአፍሪካውያን ሚስዮናውያንና እዚያው ባለችው ቤተ ክርስቲያን የሚረዳ ነበር። ሚስዮናውያኑ ወደ ሱዳን ከመሄዳቸው በፊት፥ ኮንጎ ውስጥ ከሚገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በአንዱ ይሰለጥናሉ።

ከ1935-1939 ዓ.ም. ያለው ጊዜ ለኢትዮጵያ እጅግ የሚያስጋ ነበር። ጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም. የጣሊያን ወታደሮች ከኤርትራ

ተነሥተው ኢትዮጵያን ወረሩ። ዓላማቸው ኢትዮጵያን የጣሊያን ቅኝ ግዛት ማድረግ ነበር። ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን በርትተው ቢዋጉ፥ የጣሊያንን ወራሪዎች ሊመክቷቸው አልቻሉም። ግንቦት 5 ቀን 1936 ዓ.ም. የጣሊያን ኢምፔሪያሊስቶች አዲስ አበባን ያዙ። ኢትዮጵያ ድል ስትሆን፥ የሮማው ፓፓ ለጣሊያን ጦር የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት አስተላለፈለት። ቫቲካን መልካሙንና ድል የተሞላበት ታላቅ የሕዝብ ደስታ ገለጠች። ጣሊያኖች ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠሩ፥ ወዲያውኑ ብዙ የሮም ካቶሊካውያንን ወደ አገሪቱ ላኩ። ጣሊያን ጠንካራ ካቶሊካዊት አገር ስለነበረች፥ ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠረች እዚያ ይሠሩ የነበሩ ስድስት የፕሮቴስታንት ሚስዮን ማኅበራትን ከአገሪቱ ያስወጡ ጀመር። በ1938 ዓ.ም. አገሪቱ ውስጥ የሚሠሩ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን በጣም ጥቂት ነበሩ። በጣሊያን ኢምፔሪያሊዝም ወረራ ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የቤተ ክርስቲያን እድገት በእጅጉ ተገታ። በ1943 ዓ.ም. ጣሊያኖች በተባበረው የጦር ኃይል አማካይነት ከኢትዮጵያ ሲወጡ ግን፥ ፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወደየአብያተ ክርስቲያኖቻቸው ተመለሱ።

ጦርነቱ ያስከተላቸው ውጤቶች ሁሉም ክፉ ናቸው አይባልም። የሱዳን ኢንተሪየር ሚስዮን ሚስዮናውያን በ1943 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፥ በጣሊያን ወረራ ወቅት እግዚአብሔር የሠራውን ተአምር ተመለከቱ። በ1928 ዓ.ም. የሱዳን ኢንተሪየር ሚስዮን ወላይታ አውራጃ ውስጥ ሥራ ጀምሮ ነበር። በ1937 ዓ.ም. ጣሊያኖች የሱዳን ኢንተሪየር ሚስዮንን ሲያባርሩ፥ በጥቂት የመሰብሰቢያ ስፍራዎች የሚገኙ አርባ ስምንት አባላት ብቻ ናቸው በአካባቢው የነበሩት። እነዚህ አርባ ስምንት ሰዎች የወንጌልን ቃል ያወቁና የማርቆስ ወንጌል በቋንቋቸው የነበራቸው ናቸው። ሰዎቹ መልካሙን የወንጌል የምሥራች ተግተው በመስበካቸው ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አመኑ። በ1943 ዓ.ም. አንድ መቶ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያንና 10,000 አማኞች፥ ወላይታ ውስጥ ነበሩ። ከ48 ወደ 10,000 የተገኘው ዕድገት በመቶ ሲሰላ 20,000% ነው። ይህ እድገት የተገኘው በሰባት ዓመታት ውስጥ ነበር። ፈጣን የቤተ ክርስቲያን እድገት በሚስዮናውያን ወይም በተማሩ መጋቢያን ቁጥር የሚወሰን ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን አስደናቂ ለውጥ በሕይወታቸው የተለማመዱ ክርስቲያኖች ታማኝ ምስክርነት መሆኑን እንደገና ከዚህ እንረዳለን።

## ከ1939-1945 ዓ.ም.

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እስካሁን ባጠናናቸው የአፍሪካ ክፍሎች ላይ ካደረሰው የላቀ ችግር ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ አድርሷል። ይህ የሆነበት ምክንያት የተባበረው ጦር ኃይል አባላት የጣሊያን ሱማሊያን

ለመውረርና ጣሊያኖችን ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ለማስወጣት መነሻ ያደረጉት ኬንያን ስለነበር ነው። በዚሁ መሠረት አፍሪካ ውስጥ ከተደረጉት የሁለተኛው የዓለም ጦርነቶች አንዳንዶቹ የተከናወኑት በምሥራቅ አፍሪካ ሰሜናዊ ክፍል ነበር። ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ሌላው የአፍሪካ ክልል በዚህ ጊዜ የደረሰበት የመፈናቀል ችግር ደርሶባታል። ችግሮቹን ቀደም ብለን ስለዘረዘርናቸው እዚህ አንደግማቸውም።

ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የነበሩ ብዙ የእምነት ክፍሎች በጦርነቱ ዓመታት እራሳቸውን ወደ መቻል የሚያደርሷቸው መልካም እርምጃዎች ተራምደዋል። በምሥራቅ አፍሪካ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን፥ ኬንያ ማዕከላዊ ክፍለ ሀገር ውስጥ የሚገኘው የስኮትላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን ሥራ ውጤት ናት። በ1946 ዓ.ም. በማዕከላዊ ክፍለ ሀገር የሚገኘውና የወንጌል ሚስዮናዊ ማኅበር የተባለ አነስተኛ የባፕቲስት ሚስዮን፥ አብያተ ክርስቲያኑ ከምሥራቅ አፍሪካ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዲዋሀዱ ፈቀደ። በ1943 ዓ.ም. ሙሉ ነጻነትን የሚሰጥ አዲስ መተዳደሪያ ደንብ በስኮትላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ሆነ። በመጨረሻ በ1956 ዓ.ም. ሙሉ ነጻነትና ኅብረት ተገኘና በ1961 ዓ.ም. ቻርልስ ሙሆሮ የተባለው ሰው የመጀመሪያው አፍሪካዊ አስተባባሪ ሆኖ ተመረጠ። በ1964 ዓ.ም. ደግሞ ጆን ጋቱ የተባለ ሰው ዋና ጸሐፊ ሆነ።

በኬንያ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባላት፥ አፍሪካውያን ብቻ ሳይሆኑ፥ አውሮፓውያን በተለይም በከተሞችና "ዋይት ሃይላንድስ" በተባለ ቦታ የሚኖሩ ሰዎችም ነበሩት። የዚህ ውጤቱ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን በ1921 ዓ.ም. ሁለት ቅርንጫፎችን መክፈቷ ሆነ። ከነዚህ አንዱ የአፍሪካውያን፥ ሌላው ደግሞ የአውሮፓውያን አብያተ ክርስቲያን ነበሩ። ይህ ኋላ በነጻነቱ ወቅት ተቀየረ። እንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አፍሪካውያን ጳጳሳት ለክህነት የተሾሙት በ1953 ዓ.ም. ነው። እነርሱም ፌስቶ አላንግና አባዳያ ካሪዩኪ ይባሉ ነበር። ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ያለችው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ከእንግሊዝ ነጻ የሆነችው፥ በ1960 ዓ.ም. ነው። በውጭ ያሉ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ክፍሎች (ዳዮሲስ/Diocese) የራሳቸውን አስተዳደር እስኪያቋቁሙ ድረስ በእንግሊዝ ቁጥጥር ስር ነበሩ። በዚያ ዓመት የምሥራቅ አፍሪካ ክፍለ አገር ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች። ቤተ ክርስቲያኒቱ በኬንያ፥ በታንዛኒያና በዛንዚባር ያሉ የእንግሊዝ የክልል ሰበካ ጉባኤዎችን ታቅፍ ነበር።

ኬንያ ውስጥ የምትገኘው የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን እናቷ ከሆነችው ሚስዮን ነጻ የወጣችው ወይም እራሷን የቻለችው፥ ከምሥራቅ አፍሪካ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን ወይም በኬንያ

የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ቀድማ ነው። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ከ1895-1932 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ በማውጣት ተግባራዊ አደረገው። በ1933 ዓ.ም. የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን ስያሜውን የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን በማለት ለወጠና የገንዘብ አስተዳደር ኃላፊነቱን በመውሰድ ራሱን የቻለ ቤተ ክርስቲያን ሆነ። በ1940 ዓ.ም. ለአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ የሚያረቅ ኮሚቴ ተቋቋመ። መተዳደሪያ ደንቡ በ1943 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ አለቀና የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ቤተ ክርስቲያን ስም ወደ አፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ተለወጠ። በ1952 ዓ.ም. የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ማዕከላዊ ቤተ ክርስቲያን ኮሚቴ በ1943 ዓ.ም. የተረቀቀውን ደንብ ተቀበለና የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ከአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን ሙሉ በሙሉ ነጻ ሆና ራሷን ቻለች። ከዚያም የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን ወንጌል ወዳልደረሰበት የኬንያ ክፍል ለመላክ ይችል ዘንድ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን ቦርድን መሠረተ። ዛሬ እነዚህ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ሚስዮን ቦርድ ሚስዮናውያን በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በማገልገል ላይ ናቸው። ስለዚህ ከ1952 ዓ.ም. ወዲህ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን በትክክል ራሷን የቻለች፥ የምትደግፍ፥ የምታስተዳድርና ወንጌልን የምታውጅ ቤተ ክርስቲያን ሆናለች።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ታንዛኒያ ውስጥ የነበሩት የተለያዩ የሉተራን አብያተ ክርስቲያን ራሳቸውን ወደ መቻል አምርተዋል። ቀስ በቀስ የክልል አብያተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔዎች ወይም ሲኖዶች ተቋቋሙ። እነዚህ አውሮፓ ከሚገኙት ሉተራን አብያተ ክርስቲያን አስተዳደር ነጻ የወጡ ናቸው። ምንም እንኳን ሚስዮናውያን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱን በአንዳንድ የተለዩ ተግባራት እንዲረዷት ቢጠየቁም፥ሁኔታው ከሚስዮንነት ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንነት የመለወጥ የዝግታ ሂደት የመጨረሻ ደረጃ ነበር። ሰኔ 19 ቀን 1963 ዓ.ም. የታንዛኒያ ወንጌላዊ ሉተራን አብያተ ክርስቲያን እስከተመሠረተ ድረስ እነዚህ ሲኖዶች ነጻና የተለያዩ ነበሩ። ይህ ኅብረት ታንዛኒያ ውስጥ የሚገኙ የሰባት ትናንሽ ሲኖዶች ፌዴሬሽን እንጂ፥ አንድ ቤተ ክርስቲያን አልነበረም።

ከመጀመሪያው አንሥቶ የዩጋንዳ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ትደግፍ እንደነበር ተመልክተናል። በዩጋንዳ የነበረችው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን፥ የዩጋንዳ፥ የሩዋንዳ፥ የብሩንዲና የቦጋ-ዛየር ክፍለ አገር ቤተ ክርስቲያን አካል ነበረች። ከካንተርበሪው አስተዳደር ነጻ የወጣችው በ1961 ዓ.ም. ነው።

ከ1939-1945 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ራሳቸውን የነጠሉ አብያተ ክርስቲያን እድገት ያሳዩበትና አዳዲስ ተነጣይ አብያተ ክርስቲያን የታዩበት ጊዜ ነበር። ታንዛኒያ ውስጥ ለብቻቸው የመነጠል ዓላማ የነበራቸው አብያተ ክርስቲያን የሉም። በሚገባ የታወቁት ሁለቱ፥ የመጨረሻዋ የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ትባል የነበረችውና በ1952 ዓ.ም. የተመሠረተችው፥ እንዲሁም በ1928 ዓ.ም. የተቆረቆረችው የአፍሪካ ብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

ዩጋንዳ ውስጥ ለብቻቸው የተለዩት አብያተ ክርስቲያን ጥቂት ነበሩ። ምናልባት እጅግ የታወቀችው የማላኪት ቤተ ክርስቲያን ናት። በ1913 ዓ.ም. መጨረሻ ገደማ ማላኪ ሙሳጃካዋ የተባለ አፍሪካዊ መምህር (ቀድሞ የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ማኅበር አባል የነበረ)፥ ከአንድ ዶክተሮችንና መድኃኒትን ከሚቃወም የነገድ አለቃ ጋር ተባበረ። አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ከአንድ በላይ ጋብቻን ባለማውገዟ፥ የመንደር አብያተ ክርስቲያን አባላት ቁጥር በጣም እየቀነሰ ሄደ። በ1920ዎቹ ዓመታት የቤተ ክርስቲያኒቱ ደጋፊዎች ቁጥር ከ90,000 በላይ ሆኖ ነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ክትባትንም ሆነ ለምርመራ ናሙና መስጠትን በመቃወም መንግሥትን አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ጣሉት። በዚህ ሳቢያ በ1930 ዓ.ም. የአባላቱ ቁጥር ወደ 60,000 ዝቅ አለና በ1966 ዓ.ም. ወደ አንድ ሺህ አሽቆለቆለ።

ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ሴፐሬቲስት አብያተ ክርስቲያን በሺህ የሚቆጠሩ አባላት እንዳሏቸው ይናገራሉ። በአሁኑ ጊዜ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያን ከ180 የሚበልጡ የተመዘገቡ የእምነት ክፍሎች ኬንያ ውስጥ አሉ።

## 1945-1960

የምሥራቅ አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ያደገችው ልክ በምዕራብ አፍሪካ እንደነበረችው ቤተ ክርስቲያን ነው። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ ከ1945 ዓ.ም. በኋላ ከምሥራቅ አፍሪካ ትላልቅ የእምነት ክፍሎች ብዙዎቹ ሙሉ በሙሉ ራሳቸውን ችለዋል። በዚህ ጊዜ የክርስቲያን ካውንስል በአብያተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ትብብር በማሳደጉ ተግባር ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን፥ የሱዳን ኢንተሪየር ሚስዮን ናይጀሪያ ውስጥ ያደረገውን ፈለግ በመከተል፥ "ኬሾ" እና "ቱዴይ ኢን አፍሪካ" የሚሉ መጻሕፍቶች በማሳተም ወንጌልን በጽሑፍ ማሠራጨት ጀመረ። በራዲዮ ሥርጭት በኩል የሉተራን ቤተ ክርስቲያን "የምሥራች ድምጽ" የሚባል ራዲዮ ጣቢያ አዲስ አበባ ውስጥ

በመከፈት፥ ክርስቲያናዊ ፕሮግራሞችን ወደ ብዙ የአፍሪካ አገሮች ያሠራጭ ጀመር። የአፍሪካ ኢንላንድ ሚስዮን በ1954 ዓ.ም. ለኬንያ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ የራዲዮ ፕሮግራሞችን ያዘጋጅ ጀመር። ዛሬ ቢብሊያ ሁሴማ የተባለው የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን ስቱዲዮ ብዙ ክርስቲያናዊ ፕሮግራሞችን እያዘጋጀ በቮይስ ኦፍ ኬንያ አማካይነት እንዲተላለፍ ያደርጋል።

ቤተ ክርስቲያን እራሷን ለመቻል ታደርግ ከነበረው እንቅስቃሴ አንጻር ከ1945-1960 ዓ.ም. የነበረው ወቅት ብሩህ ነበር። የወንጌል ሥራ የታገደባቸው ዋና ስፍራዎች ሁለት ብቻ ነበሩ። ከ1952-1960 ዓ.ም. ኬንያ ውስጥ የማው ማው ነጻ አውጪ ንቅናቄ የታወቀበት ጊዜ ነው። ብዙ ክርስቲያኖች በጊዜው የነበረውን ጥላቻ፥ ግድያና ለአባልነት የሚደረገውን መሀላ በመጥላት የማው ማው ንቅናቄ አባል መሆኑን አልፈለጉም። ከታች በነበረው ደረጃ በአፍሪካውያን ፖለቲከኞችና በአንዳንድ ክርስቲያኖች መካከል ከፍተኛ ጠላትነት ነበር። የዚህ ሁኔታ ምክንያት እውነታ መንፈሳዊ እንቅስቃሴው ሊሆን ይችላል። የአፍሪካ ፖለቲከኞች በመንፈሳዊው እንቅስቃሴ አራማጆች ዘንድ በከፍተኛ ጉጉት የተሞሉና ባሕርያቸው ከክርስቲያናዊነት ዝቅ ያለ ናቸው። ባሕርያቸው ከክርስቲያናዊ ብቃቶች የወረደ በማዕከላዊ ክፍለ ሀገር የነበሩ ብዙ ክርስቲያኖች በማው ማው ንቅናቄ ወቅት ተገድለዋል። በ1960 ዓ.ም. ግን እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ከ1952 ዓ.ም. ይበልጥ በረታች። ለዚህ የረዳት፥ ደካማ አባላቷ ቤተ ክርስቲያኒቱን ትተው መውጣታቸውና የቀሩት ደግሞ የክርስትና ሕይወታቸው ብርቱ መሆኑ ነው።

ሌላው እንቅፋት፥ ሱዳን ውስጥ የነበረው ሥራ አለመስፋፋቱ ነበር። ሱዳን በ1955 ዓ.ም. ነጻነቷን አገኘች። በ1958 ዓ.ም. የነበረው መንግሥት ተገለበጠ። ከዚያ በኋላ በደቡቡ የአገሪቱ ክፍል ያሉት አፍሪካውያን፥ በሰሜን ካለው የዓረብ መንግሥት እራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን ይጠይቁ ጀመር። ጥያቄውን ዓረቦቹ ስላልተቀበሉት የሽምቅ ውጊያ ዓይነት ጦርነት ተጀመረ። ዓረባዊው መንግሥትም በ1960 የሚስዮናውያንና የመጋቢያኑን እንቅስቃሴ ይገድብ ጀመር። በ1964 ዓ.ም. ክርስቲያን ሚስዮናዊያን በሙሉ ከሱዳን ተባረሩ። ከ1964-1970 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ በደቡቡ ክፍል ያሉት ክርስቲያኖች ከሰሜን በመጡ ሙስሊሞች ከፍተኛ መከራ ደረሰባቸው። ብዙዎቹ ተገደሉ። በሺህ የሚቆጠሩት ደግሞ ድንበር እየተሻገሩ ወደ ዩጋንዳ፥ ዛየር ወይም ሴንትራል አፍሪካ ሪፐብሊክ ተሰደዱ።

በ1960 ዓ.ም. ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያን ከጥቂት ጊዜ በኋላ ለሚመጣው አዲስ የፖለቲካ ነጻነት ዝግጁ ነበሩ። ቤተ

ክርስቲያን ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ ከሰማንያ ዓመታት ባነሰ ጊዜ በባሕር ዳርቻ ከነበሩ ጥቂት የአማኞች ቡድን በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ወዳሉት ታላቅ መንፈሳዊ ማኅበረሰብነት አድጋለች። እንዲያውም ከ1960 ዓ.ም. ወዲህ የተጻፉ አያሌ መጻሕፍት ዩጋንዳን "የክርስቲያን አገር" ብለዋታል። የዚህ ምክንያቱ ከሕዝቧ ከ50% በላይ በአገሪቱ ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያን የአንዱ አባል እንደሆነ ይገልጡ ስለነበር ነው። ከ1960 ዓ.ም. በፊት ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያን፥ ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ በሚስዮን ማኅበራት ላይ ይደገፉ ነበር። ከ1960 ዓ.ም. በኋላ ግን ወንጌል የማስፋፋቱን ተግባር ዳር የማድረሱን ዋና ኃላፊነት እራሷን በራሷ የምታስተዳድረው ቤተ ክርስቲያን ተረከበች።

## ጥያቄዎች

1. ከ1918-1939 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ለትምህርት ያደረገችው አስተዋጽኦ ምን ነበር?

2. በኬንያ የተባበሩት አብያተ ክርስቲያን ያልተመሠረተው ለምን ነበር?

3. "የግርዘት ውዝግብ" ምንድነው? እንዴት ተጀመረ?

4. የመንፈሳዊ እንቅስቃሴ ኅብረት ምንድነው? የተጀመረውስ እንዴት ነበር?

5. የምሥራቅ አፍሪካ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ ክርስቲያን፥ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን እና የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን እራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር የጀመሩበትን ጊዜ ይግለጡ።

6. ቤተ ክርስቲያን ደቡብ ሱዳን ውስጥ የነበራት ተልእኮ ከ1958 ዓ.ም. ወዲህ የተገታው እንዴት ነበር?

# የፖለቲካ ነጻነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት፡- ከ1960-1975 ዓ.ም.

ቤተ ክርስቲያን አፍሪካ ውስጥ ስለነበራት እድገት የምናደርገውን ጥናት ስናጠቃልል፥ በአፍሪካ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ስለሆነውና አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ገዢ መንግሥታት ተላቀው ነጻነታቸውን ስለተቀዳጁበት ወቅት እንመለከታለን። ከሰሐራ በታች ባለው የአፍሪካ ክልል የተደረገውን የነጻነት ጉዞ የመሩት፥ ሱዳንና ጋና ነበሩ። ወዲያውኑ በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ሥር የነበሩት የምዕራብና የማዕከላዊ አፍሪካ አገሮች በጥቅምት ወር 1960 ዓ.ም. ነጻነታቸውን በመቀዳጀት ተከተሏቸው። ከዚያም የእንግሊዝና የቤልጂግ ቅኝ ግዛቶች በማያቋርጥ ተከታታይነት ነጻነታቸውን ተቀዳጁ። የአፍሪካ አገሮች ሙሉ በሙሉ ነጻነታቸውን እንደተቀዳጁ፥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና የዓለም ማኅበረሰብ አባላት ይሆኑ ጀመር። እያንዳንዱ አገር የተባበሩት መንግሥታት አባል በሚሆንበት ጊዜ፥ ሰብዓዊ መብትን አስመልክቶ የማኅበሩን ቻርተር ለመደገፍ ቃል ይገባ ነበር። የቻርተሩ አንድ አንቀጽ፥ ሰዎች የሃይማኖት ነጻነታቸው እንዲከበር የሚያዝ ነው። በዚህ አኳኋን እንግዲህ እያንዳንዱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል የሆነ የአፍሪካ አገር፥ በክልሉ ለሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የሃይማኖት ነጻነት የመስጠት ግዴታ አለበት።

ከ1960-1970 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ በአብዛኛው ከሰሐራ በታች የአፍሪካ አገሮች ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በማደግ ላይ ነበረች። ይህ ክፍለ ጊዜ አብያተ ክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ እራሳቸውን የሚችሉበትን ሁኔታ ተግባራዊ የሚያደርጉበት ነበር። ነጻ የወጡት የአፍሪካ መንግሥታት ሁሉ አብያተ ክርስቲያን የወንጌልን የምሥራች እንዲያሠራጩና አብያተ ክርስቲያንን እንዲያሳድጉ ሙሉ ነጻነት ሰጧቸው። አንዳንድ መንግሥታት ያደረጉት አብያተ ክርስቲያን "በፖለቲካ" ተግባር እንዳይሳተፉ መከልከል ነበር። ይህ ሕግ ከነጻነት በፊት የተፈጠሩት ብዙ ሴፓሬቲስት አብያተ ክርስቲያን የፖለቲካ ኃይላት እንዳይሆኑ አገዳቸው። ከአገር ውስጥ ፖለቲካ አለመግባባቶችና ፉክክር ገለልተኞች እንዲሆኑም ተነገራቸው።

በዚያን ጊዜ የነበሩት አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታዎች ብሩህ ቢሆኑም፥ በአንዳንድ አካባቢዎች ግን ችግሮች ነበሩ። በ1961 እና በ1964 ዓ.ም. በነበሩት ዓመፆች ወቅት ብዙ የዛየር ክርስቲያኖች ተገደሉ። ደቡብ ሱዳን ውስጥ ዓረቦች ክርስቲያኖችን ማሳደዳቸውን ስለቀጠሉ ብዙ ሰዎች ወደ ጎረቤት አገሮች ተሰደዱ። በ1960ዎቹ የመጨረሻ ሦስት ዓመታት

ምሥራቅ ናይጀሪያ ውስጥ በተነሣው የእርስ በእርስ ጦርነት ሳቢያ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች ሞቱ፥ በመቶ የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤቶች ተደመሰሱ። አንጎላና ሞዛምቢክ ውስጥ ከፖርቱጋል ነጻ ለመውጣት በተደረገው ትግል አብያተ ክርስቲያን ብዙ ችግር ደርሶባቸዋል። የዘር መድልዎን የተቃወሙ የአብያተ ክርስቲያን መሪዎች በመንግሥት ማስፈራራት ወይም እሥራት ይደርስባቸው ጀመር።

ከ1970-1975 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ በተለያዩ የአፍሪካ ክፍሎች የሚገኙ ክርስቲያኖች ልዩ ልዩ ጭቆናዎች የተቀበሉበት ነበር። የሩዋንዳ ቤተ ክርስቲያን ዋቱትሲ እና ባሁቱ በተባሉ ጎሳዎች መካከል በተደረገው ግልጥ ጦርነት ብዙ መሪዎቿንና ተራ ምዕመናኗን አጣች። ሶማሊያ ውስጥ የነበሩት የውጭ ሚስዮናውያን፥ በአዲሱ የሙስሊም ሶሻሊስት መንግሥት ተባረሩ፥ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያንም ሥራቸውን በሕቡዕ ለማካሄድ ተገደዱ። የቻድ መንግሥት አንዳንድ የአሕዛብ ልማዶችን ወይም ባሕሎችን እንደገና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ፥ የዜጎቹን ሁሉ ተሳትፎ በጠየቀ ጊዜ፥ ክርስቲያኖች እምነታቸውን አሳልፈው ከመስጠት ይልቅ ሞትን የመረጡበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። በ1974 ዓ.ም. በኢትዮጵያ በተካሄደው የመንግሥት ግልበጣ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ኃይሏን ተነጠቀች። በቀጠሉት ዓመታት ደግሞ አንዳንድ ንብረቶቿ ተወረሱባት። ያን ጊዜ ምናልባት ከሁሉም የከፋው ስደት የተካሄደው ዩጋንዳ ውስጥ ነበር። ኢዲአሚን ሥልጣን በያዘ ጊዜ አገሪቱን ከክርስቲያናዊ ባሕል ወደ እስልምና ለወጣት። ከዓረብ አገሮች ጋር ወዳጅነት እንድትፈጥር አደረገ። በ1972 ዓ.ም. ብዙ ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ተዘጉ። በ1977 ዓ.ም. ደግሞ ከሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና ከዩጋንዳ ቤተ ክርስቲያን (የእንግሊዝ) በስተቀር አብያተ ክርስቲያን በሙሉ ታገዱ። ከ1972 እስከ 1979 ዓ.ም. በነበረው ጊዜ የዩጋንዳ ሕዝብ ሽብር ነግሦበት ነበር። ታዋቂ ክርስቲያኖች የኢዲአሚን ገዳይ ቡድን ዒላማዎች ነበሩ።

ይህን ትርጉም የለሽ ጭፍጨፋ ዓለም ሁሉ የተገነዘበው፥ በ1977 ዓ.ም. ሊቀ ጳጳስ ሉውም የተባሉት የቤተ ክርስቲያን መሪ በመንግሥት ግልበጣ ተሳትፈዋል በማለት ኢዲአሚን በከሰሳቸው ጊዜ ነበር። በዚሁ መሠረት የዩጋንዳው ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስ ተገደሉ። በተከታታይ ቀናት ደግሞ ሌሎች ብዙ ዩጋንዳውያን የርሳቸው ዕጣ ደረሳቸው። የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያኖች በሁለተኛው፥ በሦስተኛውና በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ አፍሪካውያን ክርስቲያኖች ያለፉበት ዓይነት መከራ ይገጥማቸው ጀመር።

በዚህ ዘመን በመላው አፍሪካ በነበሩ አብያተ ክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ያሳደሩ ሁለት ዋና ዋና ድርጊቶች ተፈጽመዋል። የመጀመሪያው በሚያዝያ ወር 1963 ዓ.ም. ከሠላሳ የተለያዩ የአፍሪካ አገሮች የተውጣጡ ተወካዮች ካምፓላ ዩጋንዳ ውስጥ የተሰበሰቡበት ነበር። የተሰብሳቢዎቹ ዓላማ፥ የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤን ለመመሥረትና መተዳደሪያ ደንቡን ለመቅረጽ ነበር። ተወካዮቹ የተነጋገሩባቸው ጉዳዮች፡- የቤተ ክርስቲያን ሕይወት፤ ማለት ኢኮኖሚያዊ፥ ማኅበራዊ፥ ብሔራዊና ዓለም አቀፋዊ ኃላፊነቶቿ፥ ክርስቲያናዊ ትምህርቶችና ወጣቶች፤ የቀለም ትምህርት፤ ሥነ-ጽሑፍና የመገናኛ ብዙሀን የሚሉ ነበሩ። በመጨረሻ የጉባዔው ውጤት የሆነው የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ተመሠረተና ዋና መሥሪያ ቤቱን ናይሮቢ ውስጥ አደረገ። ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ በተገኘው መረጃ መሠረት የድርጅቱ ዓላማ፡- ለመሪዎች ሥልጠና በመስጠት አብያተ ክርስቲያንን መርዳት፥ የምርምርና የጥናት ዕቅዶችን ማቅረብ፥ እና ሕልውናው እንደተጠበቀ በሙሉ ልብ ከዓለም አብያተ ክርስቲያን ምክር ቤት ጋር እና ከሌሎች ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር በጋራ በሚደረግ ስምምነት መሠረት መተባበር ነበር። ከ1963 ዓ.ም. ጀምሮ የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ከዓለም አብያተ ክርስቲያን ምክር ቤት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሺሊንጎችና የነጻ ትምህርት እርዳታ አግኝቷል። የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ዛሬ በአፍሪካ ዋና ኃይል ነው። በሚሰጣቸው በርካታ ሥልጠናዎችና ኮርሶች አማካይነት፥ የብዙ አፍሪካውያን አገልጋዮች (ካህናት) ትኩረት ስቧል።

የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ከመመሥረቱ በፊት ነው ገና ነጻነታቸውን ባገኙ የአፍሪካ አገሮች ያሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያን ወደፊት በሚያከናውኑት የወንጌል ምስክርነት አደጋ እንደሚገጥማቸው የተገነዘቡት። አደጋው የመጣው የቤተ ክርስቲያን ዋና ሥራ የሆነውን ወንጌል ለማጥፋት በፈለጉ የውጭ ኃይላት ነበር። እነዚህ ኃይላት አጠቃላይ ማኅበራዊ ጉዳዮችና ፖለቲካ የቤተ ክርስቲያንን እንቅስቃሴዎች እንዲተኩ ይፈልጉ ነበር። ይህ ሁኔታ ችግር የሚያመጣ መሆኑን የተገነዘቡና ብዙ አገሮች ውስጥ ያሉ አብያተ ክርስቲያን "ወንጌላዊ ሕብረት" መሠረቱ። ይህም እውነተኛ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ወንጌልን ለማሰራጨት የሚተባበሩበት ነው። በ1959 የሴራሊዮን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ተመሠረተ። በ1961 ዓ.ም. የላይኛው ቮልታ ወንጌላዊ ፌዴሬሽን፥ በ1962 ዓ.ም. ደግሞ የአይቮሪኮስት ወንጌላዊ ማኅበር ተመሠረተ። በ1963 ዓ.ም. ማሊ፥ ሮዴሺያ፥ ዛምቢያና ኮንጎ ውስጥ የወንጌላውያን ኅብረቶች ተመሠረቱ። እንዲሁም ከ1963 ዓ.ም.

በኋላ ሴኔጋል፥ ቻድ፥ ማላዊ፥ ናይጀሪያና ኬንያ ውስጥ ኅብረቶቹ ተመሠረቱ። እነዚህ ብሔራዊ ማኅበራት፥ አፍሪካ አህጉር አቀፍ ድርጅት እንደሚያሻት ተገንዝበው ነበር። በየካቲት ወር 1966 ዓ.ም. ከሃያ ሦስት የአፍሪካ አገሮች የተውጣጡ 192 የአብያተ ክርስቲያን መሪዎች ኬንያ ሊሙሩ እተባለ ስፍራ በመገናኘት የአፍሪካና የማዳጋስካር ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ማኅበርን መሠረቱ። ተወካዮቹ ቤተ ክርስቲያን በገጠሟት ችግሮች ላይ ለመወያየት ብዙ ስብሰባዎች ካደረጉ በኋላ፥ ለመላው አፍሪካ የሚሆን ድርጅት የሚያስፈልግ መሆኑን ተገነዘቡ። በስዋዚላንድ የባንቱ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት ቄስ አሮን ጋመዴ ይህ ጠቅላላ ሰብሰባ ጊዜያዊ አህጉር አቀፍ ኅብረት እንዲመሠርት አሳብ አቀረቡ። በዚሁ መሠረት ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቋመና 13 አንቀጽ ያሉት መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጀ። ደንቡም በተወካዮቹ በአንድ ድምጽ ጸደቀ። የኅብረቱ ዓላማ በአንቀጽ ሁለት በክፍል አንድና አራት እንዲህ ተጠቃሏል፡- "ተመሳሳይ እምነታቸውን ለሚመሰክሩ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ኅብረት ለመስጠት፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለውን የወንጌል ምስክርነት የሚያቃልሉ መንፈሳዊ ስጋቶችን በተመለከተ ክርስቲያኖች ንቁ እንዲሆኑ ለማድረግ።" የዚህ ኅብረት አገልግሎቶች፥ የወንጌል ሥራ፥ የሥነ-ጽሑፍ፥ የራዲዮ፥ የትምህርት፥ የወጣቶች አገልግሎት፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና የሴቶች ቡድኖች የመሳሰሉትን ይጨምሩ ነበር። የአፍሪካና የማዳጋስካር ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤቱን ናይሮቢ ውስጥ አደረገ። ማኅበሩ ከመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ጋር ሲወዳደር አነስተኛ ድርጅት ቢሆንም፥ የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤን ያህል ብዙ ገንዘብ ከውጭ አያገኝም ነበር። ይሁን እንጂ የአፍሪካና የማዳጋስካር ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ማኅበር እያንዳንዱ አባል ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን እንዲያስፋፉ በመርዳት ረገድ በየዓመቱ የማይናቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

በአጠቃላይ ስንመለከተው፥ ከ1960-1975 ዓ.ም. የነበረው ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በአፍሪካ እድገትና ብስለት ያሳየችበት ጊዜ ነበር። በ1974 ዓ.ም. ስዊዘርላንድ ውስጥ ሉዛን በተባለው ስፍራ ስለ ወንጌል ሥራ በተደረገው አጠቃላይ ስብሰባ፥ አፍሪካ ከየትኛውም አህጉር በላቀ ሁኔታ ክርስትና በፍጥነት የሚያድግባት መሆኗ ተመልክቷል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የምዕመናኑን መንፈሳዊ ፍላጎት ለማሟላት በይበልጥ እየሠሩ፥ በአፍሪካ ወንጌል ያልሰሙ ሰዎችንም የመድረሱ ሁኔታ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ይረዳሉ።

# ጥያቄዎች

1. የመላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያን ጠቅላላ ጉባኤ ምንድን ነው? የተመሠረተውስ መቼ ነበር? ቅርብ ግንኙነት የተመሠረተውስ ከየትኛው ዓለም አቀፍ ድርጅት ጋር ነው?

2. የአፍሪካና የማዳጋስካር ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ማኅበር ምንድን ነው? ለምን ዓላማ ነበር የተመሠረተው?

# - 33 -

# በ1994 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያን አፍሪካ ውስጥ የነበረችበት ሁኔታ

ይህን መጽሐፍ ለማጠቃለል ከሁሉ የላቀው መንገድ ቤተ ክርስቲያን በ1994 ዓ.ም. በእያንዳንዱ አገር የነበረችበትን ሁኔታ አጠር አድርጎ መመልከት ይሆናል። ክርስትና አፍሪካ ውስጥ የተጀመረው የሻማ ብርሃን ያህል ብልጭ ብሎ እንደነበር ከጥናታችን ተመልክተናል። አሁን ግን ለአንድ አህጉር ብርሃን ለመስጠትና አቅጣጫን ለማመልከት በሚችል ሁኔታ ወደ ከፍተኛ የእሳት ነበልባልነት አድጓል።

አገርዎ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል አድጋለች? ፕሮቴስታንት ወይም የሮም ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነው ሰው ቁጥር ስንት ነው? አፍሪካ ውስጥ ለሚገኘው ለእያንዳንዱ ሕዝብ ቅዱሳት መጻሕፍት በምን ያህል ቋንቋዎች ተተርጉመውለታል? መልሶቹ ከዚህ በታች ተሰጥተዋል።

ቀጥሎ የተጠቀሱት አኃዞች እራሳቸውን ሙስሊሞች፥ ፕሮቴስታንት ወይም የሮም ካቶሊኮች ብለው የሚጠሩ ሰዎችን የተቀራረበ ወይም ግምታዊ ቁጥር ነው የሚያመለክቱት። አኃዞቹ እውነተኞቹን የቤተ ክርስቲያን አባላት፥ ወይም በሃይማኖታቸው በንቃት የሚሳተፉ ሰዎችን ትክክለኛ ቁጥር የሚገልጡ አይደሉም።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተገኘው መረጃ ጊዜው ያለፈበት ስለነበር አንዳንድ መረጃዎችን "ኦፕሬሽን ወርልድ" [Operation World] ከሚለው በቅርቡ ከታተመ መጽሐፍ በደራሲው ፈቃድ ወስደናል (ኦፕሬሽን ወርልድ፥ 1999፥ በፓትሪክ ጆንስተን፥ ሕትመት በኦ. ኤም. አታሚ፥ ካርሊስል፥ ዩናይትድ ኪንግደም)።